**ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ምዝገባ ክፍት ነው**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ታዳጊ ጁንየሮችን እና ሲንየሮችን ይጋብዛል! የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በ 2021 የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ላይ (Summer RISE program) ለመሳተፍ እስከ ሰኞ፥ ኤፕሪል 26 ማመልከቻዎችን ይቀበላል።

ሠመር ራይዝ (Summer RISE) ለታዳጊ የሞንትጐመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ጁንየሮች እና ሲንየሮች በሠመር ሙያዊ ትምህርት ላይ የተመሠረተ የትምህርት ተሞክሮዎችን እንዲቀስሙ እድል የሚሰጥ ሲሆን ይኼውም ቀጣሪዎች/አሠሪዎች ተሰጥዖ/ችሎታ/ዝንባሌ ያላቸውን ለመኮትኮት ይረዳቸዋል። ሠመር ራይዝ (Summer RISE) በእጃቸው እየሠሩ የመማር እድሎችን የሚያመቻች ከመሆኑም በላይ በጁላይ ወር ተማሪዎች የሙያ ሥራ አማራጮችን ያስተዋውቃል።

ስለ ሠመር ራይዝ "Summer RISE" የበለጠ መረጃ ለማግኘት እና ለመመዝገብ ይህንን ድረገጽ ይጎብኙ፦ www.MCPS-SummerRISE.org።

**ማሳሰቢያ፦ የሠመር ራይዝ ፕሮግራሞች (Summer Programs) ምዝገባ ሰኞ፥ ግንቦት 3 ይከፈታል**

የሞንትጐመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለአንደኛ ደረጃ፣ ለመካከለኛ ደረጃ እና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሠመር ፕሮግራሞችን ይሰጣል። ፕሮግራሞቹ በሒሳብ፥ በሊተርሲ፣ በኤለክቲቭስ የባከኑ የመማር ጊዜያትን በማካካስ እና ለቀጣዩ የክፍል ደረጃ በማዘጋጀት ላይ ያተኩራሉ። የኤለመንተሪ እና የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሒሳብ፣ ሊተረሲ እና ስፔሻልስ/ኤሌክቲቭስ ፕሮግራሞችን ይሰጣሉ። የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለደጋሚዎችም ሆነ የመጀመሪያ/ኦርጅናል ክሬዲት ለሚወስዱ የመመረቂያ ክሬዲቶችን የሚያስገኙ የትምህርት እድሎችን እና እንዲሁም ክሬዲት-አልባ አማራጮችን ይሰጣሉ። ፕሮግራሞቹ፦

ያለምንም ወጪ ለሁሉም ተማሪዎች የሚሰጡ ሲሆን መጓጓዣም ይኖራል።

በሁሉም ትምህርት ቤቶች/ክለስተሮች ይሰጣል

በጠቅላላ-ቨርቹወል እና በአካል ተገኝቶ የመማር አማራጮች ይኖራሉ

**ምዝገባ ሰኞ፥ ሜይ 3 ይከፈታል።** የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራሞች ሰኞ፥ ጁን 28 የሚጀምሩ ሲሆን የኤለመንተሪ እና ሚድል ስኩል ፕሮግራሞች ማክሰኞ፥ ጁላይ 6 ይጀምራል። ተጨማሪ መረጃ እዚህ ይገኛል።

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ፈጣን የሒሳብ ኮርሶችን ይሰጣል**

ብሔራዊ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ወረርሽኙ ከመዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍሎች (K-12) ከሌሎች የትምህርት መስኮች ሁሉ በላይ በሂሣብ ትምህርት ስኬት ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የስርዓተ ትምህርትና የማስተማር ፕሮግራሞች ዲፓርትመንት በ2020 በወረርሽኙ ምክንያት የባከኑ የትምህርት ይዘቶችን ለማካካስ የረጅም ጊዜ እቅድ አዘጋጅቷል። በተጨማሪም ዕቅዱ ከቨርቹወል ትምህርት አሰጣጥ

ጋር ለማመቻቸት ሲባል የታጠፉ፣ የተቀነሱ፣ ወይም እንዲያጥሩ የተደረጉ የትምህርት ይዘቶችንና የስርዓተ ትምህርት መስፈርቶችን ጭምር ያሚላል። የብዙ አመት እቅዱ ትምህርት የሚያዳግታቸው ተማሪዎችን ፍላጎት በማሟላት ላይ ጭምር የሚያተኩር ሲሆን፣ በተጨማሪም ፈጣን ኮርሶች የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች በመለየት ትኩረት ይሰጣቸዋል። **የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከማኅበረሰቡ ለሚነሱ በርካታ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ለአንደኛ ደረጃ፣ ለመካከለኛ ደረጃ፣ እና ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፈጣን ኮርሶችን ይሰጣል።** የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ትምህርት የሚያዳግታቸው ተማሪዎችን፣ ማኅበራዊ ስሜታዊ ትምህርት የሚያስፈልጋቸውንና እንግሊዝኛ ቋንቋን የማዳበር ትምህርት የሚያስፈልጋቸውን በመርዳት ይሠራል። ስለ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሒሳብ ትምህርት እቅድ መረጃ ሜይ 25 ለትምህርት ቦርድ ስብሰባ ይቀርባል።

[ስለ ኤለመንተሪ የትምህርት ይዘት መረጃ]

[ስለ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የሂሳብ ትምህርት አጠቃላይ እይታ]

[የሁለተኛ ደረጃ ሒሳብ ቨርቹወል ትምህርት 2020-2021]

[የሁለተኛ ደረጃ ሒሳብ አተገባበር]

**አዲስ ለማህበረሰብ የቴክኒክ አገልግሎት ድጋፍ የሚሰጥ ዴስክ ፖርታል (Community Technical Help Desk Portal) ተከፍቷል።**

የቴክኖሎጂና ፈጠራ ጽ/ቤት "Office of Technology and Innovation" ማህበረሰብን የሚረዳ አዲስ ዴስክ ፖርታል/Community Help Desk portal ከፍቷል። ሠዓቱ ከሰኞ እስከ ዓርብ 7 a.m. to 5 p.m. ነው። በዚህ ፖርታል ወላጆች/ሞግዚቶች:-

- በእንግሊዝኛና በስፓንሽኛ ቋንቋዎች ጠቃሚ መረጃዎችና ማጣቀሻዎችን ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ።
- ቨርቹወል ወይም በቀጥታ የሚያገኙት ሰው ጋር ይወያያሉ
- የድጋፍ ሰጪ ዴስክ ቲኬት ካቀረቡ በኋላ አፈጻጸሙን ይከታተላሉ

ወላጆች/ሞግዚቶች ምንጊዜም ወደ communitytechsupport@mcpsmd.org ኢሜይል መላክ ወይም በቁጥር 240-740-7020 መደወል ይችላሉ፥ እና ስላቀረቡት ቲኬት አፈጻጸም በፖርታል መከታተል ይችላሉ። ወላጆች/ሞግዚቶች በተጨማሪ የት/ቤት አካውንቶቻቸውን ለማንቀሳቀስ ይህንን ድጋፍ ሰጪ መምርያ መጠቀም ይችላሉ።

**ስለ አዲስ ቨርቹወል አካዳሚ የፍላጎት ዳሰሳ መጠይቅ በፍጥነት እየመጣ ነው**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ቨርቹወል አካዳሚ (MCPS Virtual Academy) ከቅድመ መዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች ፎል ላይ ሙሉ በሙሉ የአንድ ዓመት ቨርቹወል አማራጭ ትምህርት ይጀምራል። በወረርሽኙ ወቅት ቨርቹወል ትምህርት ለብዙ ተማሪዎች አስቸጋሪ ቢሆንም ሌሎች ግን አዳብረውበታ። በኢንተርኔት የማስተማርና የመስራት ሁኔታ እንደአመቺነቱ መደረጉ በርካታ የቤተሰብ ፍላጎቶችንና የአንዳንድ ተማሪዎችን ማኅበራዊ ስሜት ፍላጎት የሚደግፍ እድል ሰጥቷል። በእነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች፣ MCPS ኦንላይን የመማር ማስተማር አማራጮችን ለመገንባት እና ለማሻሻል አቅዷል። በመጪዎቹ ቀናት ወላጆችና ተማሪዎች ስለ ቨርቹወል አካዳሚ ዝንባሌ/ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት መጠይቆችን የመሙላት እድል ይኖራቸዋል። ይህ **ስለ ቨርቹወል አካዳሚ የቤተሰብን ፍላጎት ለማወቅ ብቻ ነው እንጂ** የመቀበያ/የምዝገባ ሠነድ አይደለም። ለቨርቹወል አካዳሚ እንዴት ማመልከት እንደሚቻል ተጨማሪ መረጃ በቅርቡ ለማህበረሰቡ ይገለጻል።

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለ ESOL ተማሪዎች ምዘና ይሰጣል**

የ ESOL አገልግሎቶችን የሚያገኙ ተማሪዎች በየዓመቱ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች (ELLs) ምደባ "WIDA ACCESS" የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት መመዘኛ ቴስት/ፈተና መውሰድ ይጠበቅባቸዋል። በ 2020-2021 የትምህርት ዓመት፥ ለትምህርት ቤት ሲስተም ፈተናው/ቴስቱ ከተፈለገ ሊመረጥ የሚችል እንደሆነ ስቴቱ ወስኗል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዚህ ወቅት በእኛ ሪኮርድ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ደረጃ (ELP) 4 ላይ ተመድበው ለሚማሩ የ5ኛ እና የ8ኛ ክፍል ESOL ተማሪዎች በአካል ፈተና ይሰጣል። ትምህርት ቤቶች ይህንን መስፈርት የሚያሟሉ በአካል እና ቨርቹወል ተማሪዎችን ቤተሰቦች ለማግኘት ጥረት ያደርጋሉ።

ELP ደረጃ 4 ላይ ያልሆኑ እና/ወይም በ5ኛ እና በ8ኛ ክፍል ሳይሆኑ የ ESOL አገልግሎቶችን የሚያገኙ ተማሪዎች ወላጆች በዚህ የትምህርት ዓመት ለ ELLs መመዘኛ ተማሪዎቻቸው WIDA ACCESS እንዲወስዱ እንደሚፈልጉ እንገነዘባለን። ወላጆች ልጃቸው እንዲገመገምላቸው የመጠየቅ መብት ስላላቸው ይህን ጥያቄ ለትምህርት ቤት አስተዳደር ሊያቀርቡ ይችላሉ። ወላጆች ልጃቸው ምዘና እንዲወስድ/እንድትወስድ ጥያቄ ማቅረብ የሚችሉት እስከ ሜይ 14 ነው። ትምህርት ቤቶች ትምህርት እንዳይስተጓጎል በረቡዕ ዕለት ምዘናውን ለመስጠት ይጥራሉ። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች መጓጓዣ ይሰጣል። በትምህርት ቤት ደረጃ የፈተና መስጫ ጊዜ ሠሌዳ ከተዘጋጀ በኋላ ስለ መጓጓዣ ፕሮግራም ዝግጅት ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ ዝርዝር ይሰጣሉ።

**ከሜይ 8 - 22 "Remake Learning Days" ይካሄዳል**

"Remake Learning Days Across America (RLDAA)" ማለት በማህበረሰብ ውስጥ በርካታ የትምህርት እድሎች የሚከበሩበት ክብረ በዓል/ፌስቲቫል ነው። በመላው አገሪቱ 17 የተለያዩ ሪጅኖች ላይ የሚከበረው ይህ ክብረ በዓል ለወጣቶች የፈጠራ ዝንባሌ፣ ጽናት፣ እና ጉጉት እንዲያዳብሩ የፈጠራ ተሞክሮዎችን እና እድሎችን በትኩረት ያቀነቅናል።

በ ዲ.ሲ፥ በሜሪላንድ እና በቨርጂኒያ አካባቢዎች ትምህርት ቤቶች፣ ቤተ መጻሕፍት፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች፣ ቢዝነሶች እና የማኅበረሰብ ማእከሎች የመሳሰሉትን ጨምሮ— በርካታ ድርጅቶች በመተባበር ለወጣቶችና ለቤተሰቦች ከፍተኛ ጥራት ያለው የትምህርት ተሞክሮ ለመስጠት እየተዘጋጁ ናቸው። እነዚህ ክንውኖች በእጃቸው እየሠሩ የሚማሩባቸው ስለሆኑ ለወጣቶችና ለቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ለተንከባካቢዎቻቸው ጠቃሚና፣ አግባብነት ያላቸው የትምህርት ተሞክሮዎችን የሚሰጡ ናቸው። አብዛኞቹ ክንውኖች በሁሉም እድሜ ለሚገኙት ነጻና ክፍት ናቸው።

በዚህ በይነመረብ ላይ የበለጠ መረጃ ይገኛል፦ https://remakelearningdays.org/dmv/